DISTRICT OF COLUMBIA
PUBLIC SCHOOLS

# በSY23-24 የኩሌጅ (Coolidge) ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ውስጥ የቅድመ ኮሌጅ አካዳሚ: የመግቢያ ሂደት የደረጃ መጠን (Admissions Process Rubric)

ለክፍል ደረጃዎች፡ 9 እና 10

**ስለ ቅድመ ኮሌጅ አካዳሚ የመግቢያ (Admissions) መስፈርት**:
የቅድመ ኮሌጅ አካዳሚ በኩሌጅ (Coolidge) ውስጥ፣ **COLTS** መሆን የሚፈልጉ ምሁራኖችን ይፈልጋል:

> የቀለም ትምህርት ግቦቻቸውን ለማሳካት እና ፈታኝ በሆኑ ነገሮች ውስጥ ጥብቅነትን እና በጽናት ራስን ማስተካከል የሚጠይቅ **ቁርጠኝነት (Committed)**።
> ስለነርሱ እና ስለእኩዮቻቸው የማደግ ችሎታ **ብሩህ አመለካከት ያላቸው (Optimistic)።**
> ታማኝነትን፣ ተጠያቂነትን፣ እና የትምህርት ቤታችንን ማህበረሰብን እሴቶችን **መሪዎች በመሆን (Leader)**የሚሸከሙ።
> በሚያደርጉት እርምጃዎች ላይ አስተዋይ በመሆን እና በዓለም ላይ አዎንታዊ አስተዋጽዖ ለማምጣት በመስራት **ህብረተሰብን መቀየር (Transforming Society)።**

**ስለ ቅድመ ኮሌጅ አካዳሚ የመግቢያ (Early College Academy (ECA) የመግቢያ (Admissions) ሂደት:**
የመቀበያ ሂደታችን የሚያካትተው ሁሉን አቀፍ የሆነ ምልከታ ለእያንዳንዱ የማመልከቻ ክፍሎች - ሪፖርት ካርዶች፣ ጽሁፍ (essay)፣ እና የአስተማሪ ድጋፍ መስጫዎች (recommendations)። እያንዳንዱ የማመልከቻው ክፍሎች፣ ከዚህ በታች በሚገኘው ሰንጠረዥ መሰረት ተገምግሟል። ምንም አንድ ክፍል፣ ብቻውን ለብቁነት መወሰኛ ሆኖ አይወሰድም። በቀለም ትምህርት ፕሮግራም ጥብቅነት ምክንያት፣ በGPA ላይ ከፍተኛ አፅንዖት የምንሰጠው እና በቀለም ትምህርት እድገት ላይ ወደላይ ሲያሻቅብ ማየትን የምንመርጠው ይሆናል። በጣም ስኬታማ ሆነው ያገኘናቸው አመልካቾች፣ ፈታኝ-ለሆነ ስራ ቁርጠኝነት ያላቸው ሲሆን ይህንንም በጽሁፋቸው (essay)፣ በድጋፍ መስጫዎች (recommendations) እና በቤተሰብ ቃለ-መጠይቅ በተጨማሪነት ማስመስከር የቻሉ ናቸው።

የቤተሰብ ቃለ-መጠይቅ፣ የመጀመሪያ የሆነ ግንኙነቶችን የምንገነባበት እና በማመልከቻ ሌሎች ገጽታዎች ላይ ጎልተው ለመመልከት ያልቻልናቸውን ነገሮች ለማወቅ እድል የሚሰጠን ነው። ለቃለ- መጠይቁ፣ የቤተሰብ አባል፤ ወላጅ፣ ሕጋዊ አሳዳጊ፣ ወይም ሌላ ቅርብ የቤተሰብ አባል ሊሆን ይችላል። ተማሪዎችን በመደበኛነት የሚረዷቸው፣ ሌላ በተማሪው ህይወት ውስጥ ጉልህ አስተዋጽዖ ያለው ሰው፤ እንደ አሰልጣኝ፣ አማካሪ፣ ወይም የሕይወት መሪ/mentor፤ ሊሆንም ይችላል። የቃለ-መጠይቁን ጨርሰን ስምወጣ፣ የተማሪውን ማንነት በተሻለ ሁኔታ የምንረዳበት እና ቤተሰቡ እንዴት መማርን እንደሚደግፉ ለማወቅ እንደሚያስችለን ተስፋ አለን።

DISTRICT OF COLUMBIA
PUBLIC SCHOOLS

እያንዳንዱ የማመልከቻ ሂደት ክፍሎች፣ ከዚህ በታች በሚገኘው ሰንጠረዥ መሠረት የደረጃ ውጤት (scored) የሚሰጠው እና የሚለካ ይሆናል። ሊገኝ-ከሚችለው ከ100 ውስጥ፣ 85 ነጥቦችን ያገኙ አመልካቶች ብቁ ይሆናሉ፤ ሆኖም ይህ ቁጥር ሁሉን-አቀፍ በሆነው የአመልካቾች ምልከታ ላይ መሠረት በማድረግ፣ ዓመታዊ የዝቅተኛ ደረጃ የሚስተካከልበት ሁኔታ ሊኖር ይችላል።

| **የመግቢያ (Admissions) ክፍሎች** | **መለኪያ (Weight)** | **ማስታወሻዎች፡** |
|---|---|---|
| የቀለም ትምህርት የመስፈርት ምልከታ (GPA) | 40 ነጥቦች | ECA ውጤቶችን (GPA) እንደ የቀለም ትምህርት መስፈርት ምልከታ አንዱ አካል አድርጎ ይመለከተዋል። በአነስተኛነት መገኘት የሚገባው (minimum) የGPA መስፈርት የለም። ተማሪዎች፤ ለSY21-22 የመጨረሻ ሪፖርት ካርዳቸውን ማስገባት እና ለSY22-23 የመጀመሪያ ተርም ሪፖርት ካርድን ማስገባት አለባቸው። የሪፖርት ካርድ/የትምህርት ውጤት ማረጋገጫ እና ውጤቶች፣ ለማመልከቻው የመግቢያ (admission) ሂደት ከግምት ውስጥ እንዲገቡ መግባት አለባቸው።<br><br>ከELA፣ ሳይንስ፣ ሂሳብ እና ECA/ታሪክ ውስጥ ያሉ ክፍሎች፣ GPAን ለማስላት ጥቅም ላይ የሚውሉ እና፤ በECA የ3.0 ነጥብ GPA ወይም ከዚያ በላይ የሆነ ነጥብ ያላቸው በተለመደ ሁኔታ ስኬታማ የሆኑ ተማሪዎች ናቸው። |
| ድጋፍ መስጫዎች (Recommendations) | 20 ነጥቦች | ECA፣ 2 የድጋፍ መስጫዎች (recommendations) ይፈልጋል። ECA፣ የአስተማሪ ድጋፍ መስጫዎችን (recommendations)፣ ለተማሪዎች የአካዳሚክ መዝገብን፣ የጥረታቸውን ደረጃ፣ እና አጠቃላይ በትምህርት ቤት ውስጥ ያላቸውን ተሞክሮ ይዘትን ለመስጠጥ ይጠቀምበታል። በየግል የገቡ የድጋፍ መስጫዎችን (recommendations) በራሳቸው በኩል እንዲከታተሉ እና የድጋፍ ሰጪው የተማሪውን በእጅጉ የተሟላ ምስል እንዲያስገቡለት ለማድረግ፤ ተማሪዎች እና ቤተሰቦችን ክትትል እንዲያደርጉ አጥብቀን እናበረታታለን። ሆኖም፣ ተማሪዎች ላልተሟሉ ወይም ለጠፉ የድጋፍ መስጫዎች (recommendations) ቅጣት አይደርስባቸውም፤ |

| | | |
|---|---|---|
| | | ስለሆነም፤ በተገኘው የድጋፍ መስጫዎች (recommendations) ላይ መሠረት በማድረግ ቀጥሎ እንዲገመገም ይደረጋል። |
| የጽሁፍ ናሙና (Writing Sample) | 25 ነጥቦች | የጽሁፍ ናሙና (writing sample)፤ የተማሪን ፍላጎት እና የችሎታ ደረጃን ለማግኘት ይጠቅማል። የመቀበያው (admissions) ቡድኑ የተማሪውን በECA ውስጥ ያለውን ፍላጎት፣ ለመማር ያለውን ቁርጠኝነት፣ እና የወደፊት ግቦችን ለመለካት ጽሁፉን (essay) ይመለከታል። የመፃፍ ናሙና (writing sample) በተጨማሪም - እንደ የተማሪው ሰዋሰው (grammar)፣ ቃላት (vocabulary) እና ቴክኒካል የአፃፃፍ ደረጃ፣ የመጀመሪያ ናሙና ሆኖ ጥቅም-ላይ ይውላል። |
| የቤተሰብ ቃለ-መጠይቅ | 15 ነጥቦች | ECA፣ ተማሪዎች ወደ ቃለ-መጠይቁ፤ ከቤተሰብ አባል ጋር (ከወላጅ፣ ሕጋዊ አሳዳጊ፣ የቅርብ የቤተሰብ አባል) ወይም ሌላ በህይወቱ ውስጥ ጉልህ አስተዋጽዖ ያለው ሰው ጋር (እንደ አሰልጣኝ፣ አማካሪ፣ ወይም የሕይወት መሪ/mentor)፤ ተማሪዎችን በመደበኛነት ከሚረዷቸው ጋር አብረው እንዲካፈሉ ይፈልጋል።<br><br>በጤና መመሪያ እና በቤተሰብ ሁኔታዎች ላይ መሠረት በማድረግ፣ በSY23-24 ውስጥ፣ የቃለ-መጠይቁ በርቀት (virtually)፣ ሊከናወን ይችላል። የጤና መመሪያን በመከተል እና በመቆጣጠር ላይ፣ ቁርጠኛ ሆኖ መስራቱን - DCPS ይቀጥልበታል። |